እኛና አብዮቱ በፍቅረሥላሴ ወግደረስ

ሦስተኛውና የመጨረሻው ግምገማ፣

በታደለ መኩሪያ

ከምዕራፍ 13-19 ወይም ከገጽ221-440 ያለውን እገመግማለሁ።



በምዕራፍ 13 በመጀመሪያው ገጽ ላይ ሰለ ድርጅትና ሰለአባላት በሰጡት ትንታኔ ልጀምር፤ "ምንም አደጋ የማይጋብዝ እስከሆነና አነስተኛ መስዋዕት እነኳን የማይጠይቅ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ብሎም መጠነኛ ጥቅም እነደሚያስገኝ ከታወቀ የፓርቲ አባልነትን ይወዱታል። በአጋጣሚ ግን በአባልነት የተሰባሰቡበት ድርጅት ከመንግሥት ጋር ቢቃቃር በሕብረት ቆመው ከመታገል ይልቅ ይሸሹታል። በነፃነት መደራጀትን የሚከለክል መንግሥት ፍፁም አምባገነንና ፀረ-ዲሞክራሲ ሰለሚሆን ተደራጅተው ለመታገል የሚፈልጉ የነቁ ምሁራን ይታሠራሉ፣ ይገደላሉ፣ ይሰደዳሉ።ይህም ሆኖ ግን የሕዝብን መብት ለማስከበር ሲሉ በጣም ጥቂቶች ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው በህቡዕ ይደራጃሉ፣በህቡዕ ሕዝቡን ይቀሰቅሳሉ፣ለአመፅም ያነሳሳሉ፣ከፖለቲካው ሥራ አልፈውም የትጥቅ ትግል ያካሂዳሉ።" የደራሲው ትንታኔ ከ1966 ዓም በፊት በሀገራችን ምንም ዓይነት የተደራጀ የፖለቲካ ፓርቲ አለመኖሩን ለማሣየት በወቅቱ በካድሬዎችና በደርግ አባሎች በሰፊው ሕዝብን ይቀሰቅሱበት የነበው ግባት ነው። ለደርግ አባላት እናንተሰ ከየትኛው ትመደባለችሁ ሲባሉ መልሳቸው 'ደም አደር' ነበር፤ ሆኖም ግን ከ1966 ዓ ም በኋላ ብዙ ድርጅቶች ተመስርተዋል፤ ከትንታኔያቸው ሦስት ባሕሪያት እናያለን ፣ አደርባዮችን፣ አምባገነኖችንና ቆራጥ ታጋዮችን፤ ደራሲው ከዘረዘሯቸው ስድስት የፖለቲካ ድርጅቶች እርሳቸው አባል የሆኑበት ድርጅት ሀገር አስተዳድሯል። ስለዚህ ሌሎችን ድርጅቶች በልማቱም ሆነ በጥፋቱ ብዙም ድርሻ አልነበራቸውም፣ ደራሲው የጥፋቱ አካል አድርገው ሰለአቀረቧቸ ትክክልኛውን ግንዛቤ መጽሐፉን ላነበቡ ሁሉ ለማቅረብ እሞክራለሁ፤ በወቅቱ የጠቀሷቸው ድርጅቶች እነዚህ ነበሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፤የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቅ (መኢሶን)፤ወዝአደር ሊግ (ወዝሊግ)፤ማርኪሲስት ሌኒኒስት ሪቮሊሽነሪ ድርጅት (ማሌሪድ)፤ አብዮታዊ ሰደድ (ሰደድ)፤የኢትዮያጵያ ጭቁኖች አበዮታዊ ትግል (ኢጭአት) ደራሲው ሰለ ኢሕአፓ የሰጡት ትንታኔ በእርግጥ ለወጣቱ ትውልድ ትክክለኛውን ታሪክ ለማስተማር ከተነሱበት ዓላማ ጋር ይጣጣማል ወይስ አይጣጣምም እስቲ አብረን እንየው፤ ምዕራፍ 14ና ምዕራፍ 15 ባጠቃላይ የሚገልጸው ሰለኢሕአፓ ነው። ከገጽ 243 -333 ዘጠና ገጾችን ይሸፍናል፤ እነደካርታ ጫወታ ማሸነፊያ ጆከር ወይም ሰበዝ ባብዛኛው የመጻፉ ገጾች ውስጥ ኢሕአፓ የሚለው ቃል ተሰግስጓል። ሰለ ኢሕአፓ ደራሲው ያቀረቧቸውን ኩነቶች በአምስት ከፍያቸዋለሁ፤ በቀላሉ እውነቱ የት እንዳለ ለማየት እንዲያስችል ነው።

አብዮተኞችን መግደል፣ ሴቶችን ለሴተኛ አዳሪነት ማስኮብለል፣ የኤኮኖሚ አሻጥር፣ በደርጎቸ ውስጥ ሁከት መፉጠር፣ ሀገር ማስገንጠልና ከውጪ አገር መንግሥት ጋር ማበር ናቸው፤

አብዮተኞችን መግደል፣ ከገጽ 275-296 ውስጥ 271 አብዮተኞች በኢሕአፓ መገደላቸውን እናያለን፣ ወደ ዝርዝሩ ከመግባቴ በፊት ደራሲው በገዛ ብዕራቸው ገጽ 84 ላይ የጻፉትን አብረን እንየው፣ አሸከሮች፣ ዘበኞች፣ገረዶች መረጃ ይሰጡናል፤ መሣሪያ፣ገንዘብ፣ንብረት ወደ ሌላ ቦታዎች ማሸሻቸውን ይጠቁሙናል፤ 'እኛ እስከ ዛሬ የበይ ተመልካች ነበርን፣ ዕድሜ ለእናንተ እንጀራ ሊወጣልን ነው! ከእናንተ ጎን ተሰልፈን አቆርቋዦችን እንታገላለን፣ በማንኛው ጊዜ ትዕዛዝ ብትሰጡን ለመፈጸም ዝግጁ ነን! ከጅመሩ የምቀኞች አብዮት አስመስሎታል። ደርግ ነጉሡን ለማውረድ፣ ስልሳዎቹን ለመግደል፣ የመሬትን አዋጅ ለማወጅ ሕዝቡ ደገፈኝ ይል የነበረው እነዚህን እያዳመጠ ነበር፡፡ እነርሱም ከነዚህ የተሻለ ግንዛቤ

አልነበራቸው፤ ለሰፈርተኛው ኗሪዎች፡ ወፍጮ ቤት ተላላኪዎች፣ የድግስ እንጨት ፈላጮች፣ ጌሾ ወቃጮች፣ ውለው አድረው፣ ለቀበሌ ሊቀመበርነት ለአብዮት ጠባቂነት በየመሥሪያ ቤቱም የተሰገሰጉት ይህ መሰል ሰዎች ነበሩ። በቀበሌዎች ተመርጠው አባወራውን በአቆርቋዥ ስም አሣስረው፣ ልጆቻቸውን በኢሕአፓ ስም ጦቁመው ከቀድሞ እመቤቶቻችው ጋር አልጋ ልውጣ ሲሉ ዝም ማለቱ ይበጅ ነበር ነው የሚሉት? የቤተሰባቸው ጥቃት የተሰማቸው ልጆቻቸው ለመበቀል የቀበሌውን ተመራጭ ተኩሰው ቢገድሉት ተጠያቂው ማነው? ሀገር እመራለሁ የሚለው መንግሥት ሀገሪቱን ሕግ አልባ አድርጎ፣ የዜጎችን ደህንነት ከማስጠበቅ ይልቅ ራሱ ገዳይ ከሆነ፣ ተጠያቂው ማነው? ሌላው ደግሞ የኢሕአፓ መፈክር የሆነውን 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም' በማለት ለሕብረተሰቡ ቅስቀሳ ሲያደርጉ በህቡዕ፣ ወረቀት ሲበትኑ የያዟቸውን ወጣቶች ሲገርፋቸውና ሲያጉሏሏቸው ፣ ከዚህ እንዲታቀቡ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተልኮላቸው አሻፈረኝ ብለው ጥቆማውንም ግድያውንም በማንአለብኝ የገፉትን፤ በመግደላቸው የተሾሙትን፣ ከጥቆማም አልፎ 'ነፃ እርምጃ' የወሰዱትን፣ ኢሕአፓም ባሰማራቸው እስኳዱ አባላቱን ባስገደሉበት ግለሰቦች ላይ ግድያ ፈጽሟል፤ ደራሲው ትንሽ ሚዛናዊ ለመሆን እንኳን አንድም በመንግሥታቸው ታጣቂዎች የተገደለ የኢሕአፓ አባል ስም አልጠቀሱም፤ ቢፈልጉ የስም ዝርዝራቸውን ከየቀበልዎች ማግኘት ይችሉ ነበር፤ ኢሕአፓ የገደላቸውን በሺዎች ብለው ከጠቀሱት የ271 ዱን በዝርዝር ሲያቀርቡ ማለቴ ነው። የከፍተኛ 12 ኗሪው ብረሃኑ ሙሉጌታ ሃያ አራት ንጹሃን መግደሉን ገጽ 274 ገልጸዋል፤እዚህ ላይ ሰለድርጅቱ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንደሌላቸው አያለሁ፤ ሁለት መረጃዎችን ልስጥ፣ በድብደባ ብዛት ወጣቱ ከዚያም በላይ ገደልኩ ሊል ይችላል፣ ሁለተኛ የ አንድ የቀበሌ ሊቀመበር ሲገደል በክፍተኛው ባሉ ቀበሌዎች በሙሉ ከታሰሩት ውስጥ ቀደኛ ኢሕአፓ አባል የሚላቸውን በድብደባ ገለናል አሰኝተው ይገሏቸዋል፤ በመፍክራቸውም አስቀምጥውታል፣ 'አንድ አብዮተኛ ቢሞት በሺ ፀረ-አብዮተኛ' በማለት ተፎክሯል፤ ደራሲውም 'ዲሞን በዲሞፍትር' ሲሉ ገልጽውታል፤ይህ ወጣት አንድም ገደለ፣ ሃያም ገደለ፣ ወረቀት በተነ፣ ሞት አይቀርለትም፤ ሰለዚህ ሌሎች ጓዶችን ለማዳን ከጠቀሱት ቁጥር በላይ ገድያለሁ ሊል ይቻላል፤ ሰለ ድብደባ ከተነሣ ያየሁትን ልናገር፣ ከፍተኛ ሃያ ፔፕሲ ማዞሪያ የኤልትክ ዕቃዎች መለዋወጫ መጋዘን የነበርው የከፍተኛው ሃያ እስር ቤት ውሰጥ አንድ ወጣት ሲደበደብ ቤታችን ውስጥ አልጋው ሥር ታንከ ተቀብሯል ማለቱን በውቅቱ በአካባቢው በሰፊው ይወራ ነበር፤ ከዚህ የምረዳው የድርጊቱን ኢሰዕባዊነት ነው ። ይህም የሆነው የካቲት 1970 ዓ ም ነበር፤ ሌላው ደግሞ በገጽ 274 ላይ የ12 ዓመት ሕፃን ኢሕአፓ የላከው፣ ሰው ገድሎ እማማ ብሎ አለቀሰ ብለዋል፣ ፣ ለባብሌ ቶላ ግድያ ማስተባበያ እንደሆነ ግልጽ ነው። ፤ ደርግ ሕፃኑን ባብሌ ቶላን የኢሕአፓ አባል ብሎ በገደለበት ወቅት ትልቅ ተቃውሞ አስነስቶበት ነበር፤ ኢሕአፓም የደርግን ማንነት ለማጋለጥ ትልቅ የፖለቲካ ቅስቀሳ ሰርቶበታል። በገጽ 270 ላይ ስለርዕሰ መምህሩ ፍቃዱ ኡርጋ አገዳደል የተረኩት ትረካ በፍጹም በማንም ሕብረተሰብ ውስጥ የሚደረግ አይደለም፤ አቶ ፍቃዱን ለማስገደል በር ያስከፈተቻቸው ጎረቤታቸው በግል ለኢሕአፓ ትተባብራለች እንበል ግን ቤተሰቧ ላይ መነግሥት የሚወስደውን እርምጃ አታውቅም ማለት ይቻላል? በዚያ ላይ ቤተሰቧና ሕብረተሰቡ እንደሚቃቃር እያወቀች በገሃድ በር አስከፍታ ጎረቤቷን አታስገድልም፤ ይህ ይሆናል የሚል ካለ የራሱ ግንዛቤው ነው፣ ደራሲውም ግንዛቤያቸው ያ ነው፤ ? እውነት ከሆነ የአቶ ፍቃዱ ሞት ያሣዝናል፤ ደራሲው እንዲህ ልባቸው ለሰው ልጆች የሚደማ ከሆነ ' ነፃው እርምጃ' እየተባለ ለሚጠራው የግድያ ተግባር ያሰማሩት አረመኔው ግርማ ከበደ የብረሃነና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ የነበረችውን ነፍሰ ጡር ዳሮ ነጋሽን መግደሉን እንዴት ረሱት? የአዲስ አበባ ሕዝብ አይረሳውም፣ በወቅቱም ድፍን የአዲስ አበባ ሕዝብ ሰምቶት መንግሥታቸውን በመቃወም ሰላማዊ ሰለፍ ወጥቶ ነበር፣ እንጦጦ ያውም ሌሊት በመምህር ፍቃዱ ኡርጋ ላይ የተፈጸመውን ግድያ በዝርዝር ሲያቀርቡት፣ በጠራራ ፀሐይ አራት ኪሎ ከመሥሪያ ቤታቸው በራፍ በዳሮ ነጋሽ ላይ የተፈፀመውን ግድያ አልሰሙትም፤ በወቅቱ ሕብረተሰቡ በግለጽ የሚያውቀውን ክዶ የእኔን ዕወቅልኝ ቢሉት አያዳምጥም፣ በመጻሐፉ ውስጥ የተገለጹት ኩነቶች ከምር ለመውሰድ ይጠራጠራል፡፡ ከግድያው ጎራ ሳልወጣ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ከሐምሌ 1969-1971 ዓ ም የነበረውን ሁኔታ በወፍ በረር መልክ ላሳያቸሁ፣ በሃያ አምስቱ ከፍተኞች፣ ከዘጠና የማያንሱ ቀበልዎች ውስጥ በኢሕአፓ የተጠረጠሩት እንደ ድርጊታቸው ክብደት ይታሰራሉ፤ እነዚህ ተጠርጣሪዎች በድብደባ የገደሉም ያልገደሉም ገለናል አሰኝተዋቸው በታይፕ በተፃፈ ሰነድ ላይ ያስፈርሟቸዋል፤በሌላ ቀበሌ የተገደለ የቀበሌ ሊቀመበር ወይም አብዮት ጠባቂም ከኖረ ባልነበሩት አካባቢም ቢሆን ገድያለሁ ብለው እንዲፈርሙ ይደረጋሉ፣ ወጣቶቹን ለአራት ለአምስት ጊዜ ካሰቃዩአቸው በኋላ ነው ገድያለሁ ብለው የሚፈርሙት፣ ሌላ ጠቋሚ ካልመጣ ይህንን ሁሉ ሥቃይ ተቋቋመው የሚድኑም ፣ የሚገደሉም ነበሩ፤ ገዳዮቹ ሌለት በስምንት ሰዓት ላይ በጫት መርቅነው፣ በመጠጥ ሰክረው ይመጣሉ፣ በመጋቢት ወር 1970 ዓ ም በከፍተኛ ሃያ ቀበሌ 40 ነበር። ሃያ አራት ወንዶችና አራት ሴቶች ውስጥ አሥራ ሁለት ወጣቶችን ለመግደል ይወሰዳሉ፣ ገዳዮቹ የአባቶቻቸውን ስም ባላስታውስም፣ ፍሬው፣ ማስረሻ፣ እና ገበረመድህን ይባላሉ፡፡ የከፍተኛውን ካድሬ ስም ተዘነጋኝ፣ የከፍተኛ ሁለትና የከፍተኛ ሃያ ካድሬ ነበር። ግድያው ከቀበሌው አጥር በር ላይ ተጀመረ፤ ቸሩ ነበር፣ የተገደለው፣ ቸሩ የኮከበ ጸባሃ ሁለተኛ ደረጃ መምህር ነበር፣ ለማንበብ

መጽሐፍ ካነሣ ገጾቹ ቢበዙም በአንድ ቀን ፉት ይለዋል፤ ከመገደሉ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ዓለም አቀፋዊ የሴቶች ቀን (March 8) ለማክበር ሴቶች እህቶቻችን በዐሉን የሚመለከት ጽሑፍ እንዲዘጋጅ ጠየቁ፤ እኔና ቸሩ ሐላፊነቱን ወስደን ሰለነበር ሰለሕብረተሰባችን እጅግ የታመቀ ዕውቀት እንዳለው የተረዳሁት ያኔ ነበር፣ 'ድርብ ጭቁኗ' በሚል ርዕስ በድራማ መልክ አዘጋጅቶ፣ በምን ይታጀብ ሲባል? ቸሩ ጊዜ አለወሰደበት 'አምጭልኝ እህቴ' የሚል ግጥም ጽፎ ዜማ አወጣለት፤ ሁሉንም ሥራ ያቀነባበረው ቸሩ ነበር ። አራቱ ሴቶችና ስድስት ወንዶች ተሳታፊ ሲሆኑ የቀረነው ተመልካች ሆንን፤ ደራሲው ሰለድርጅትና አባላት በሰጡት ትንታኔ ውስጥ ሰለንቁ ምሁራን የሰጡትን ትንታኔ ቸሩ ያሟላዋል እላለሁ፤ ቸሩ ለመገደል ሲወጣ አንዱ ገዳይ የለበሰከውን ኮት አውልቅ ሲለው 'ለሀገሬ ከዚህ የተሻለ ነገር ትቼላት የምሄደው ይኖኝ ይሆን? አወልቃለሁ፣' የመጨረሻዋ ቃሉ ናት፤ የተገደለው በእውቀቱ ልቆ በመገኘቱ ብቻ ነበር። አሥራ አንዱ እጃቸው እንደታሰረ በአውራ መንገዶች ላይ በጥይት ተደብድበው ተገደሉ።

ኢሕአፓ ሴቶቹን ለሴተኛ አዳሪነት ማሰማራቱንና ማስኮብለሉን፣ ከገጽ 257-258 ታገኙታላችሁ፣ ደራሲው ኢሕአፓ ያልደረሰበት የሕብረተሰቡ ክፍል እንደሌለ በሰፊው በመጻፋቸው ውስጥ ገልጸውታል፤ ሰለዚህ የቡና ቤት ሠራተኞችን፡ ወጥ ቤት ሠራተኞችን፣ አልጋ አንጣፊዎችን፣ ዘበኞዎችን፣ መጠጥና ምግብ አቅራቢ ሴቶችንም እንደማንኛው ሰው እኩል መብት እንዳላቸው አስተምሯል፤ ይህን ያስተምረ ድርጅት ሴቶችን ለገንዘብ ለወሲብ ሥራ አሰማራ ሲሉ በማስረጃ አስደግፈው አይደለም፡፡ ኢሕአፓም ሆነ ሌሎቹ ግራ ዘመም ድርጅቶች በሴቶች መብት ጥያቄ ላይ የማያወላውል አቋም አላቸው። በሃምሣዎቹ ለሸቀጥ ማራገፉያ ለባህል ብረዛ ሴቶችን ሚኒሰከርት የሚባለው ቀሚስ አልብሰው የፋሺን ሾ ተብሎ በጊዜው የቀዳማዊ ሃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሲቀርብ ተማሪዎች ያስቆሙት በገማ ዕንቁላል በመዋጋት ነበር፣ የዚያ ትውልድ አካል የሆነውን ኢሕአፓን ሴት ጓዶቹን ለወሲብ አሰማራ ብለው እንደ (pimp) መቁጠሩ፣ ውኃ አያነሣም፤ በኢሕአፓና በደርግ መካከል የማይታረቅ ቀራኔ ቢኖርም በመጽሐፍ መልክ አንድን ድርጅት ለማጋለጥ ሲባል ቆራጥ ሴቶች የዋሉበትን ውሎ አፈር አልብሶ ለወሲብ ተሰማሩ ማለት በጣም ያሣፍራል፣ የወሲቡ ጉዳይ ከተነሣ ከ66 አብዮት እሰከ 1972 ዓ ም ባሉት ዓመታት መካከል የወጣቱ አዝማሚያ ምን ይመስል ነበር? ከ1972ዓ ም ኢሕአፓ የከተማውን የፓለቲካ እንቅስቀሴ ካቆመ በኋላስ ? ይህንን የሀገሪቱ ዜጎች ይፍረዱት፤ አሁን በአለም ዙሪያ በሴት እህቶቻች ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃ ደራሴው ይመሩት የነበረው መንግሥት ጥንስስ ነው፤ ሌላው ቀርቶ መንግሥት አለን ብለው የሀገር ሕልውና ለማስከበር በጅግንነት የሞቱ ጅንራሎችና ባለሌላ ማዕረግ ወታደሮች ልጆች በየበረሃው ተደፍተው ቀርተዋል፣ ውጭ አገር የወጡትም ቢሆኑ ያለፉበት ሰቆቃ ሁኔታ ብዙም በሕይወት እንዲኖሩ አላደረጋቸውም፤ በደራሴው ጠቅላይ ሚንስትርነት የታየው፣ የደርግ አባሎችና ካድሬዎቻቸው በአዲስ አበባና በየክፍለሃገራት በሴቶች ላይ የፈጸሙትን በደል ለመግለጸ መጽሐፍ ያጽፋል። በገደሏቸው ሹማምቶች ቤተሰብና ሴት ልጆቻቸው ላይ ያደረሱትን ሆድ ይፍጀው፣ ድፍን ያአዲስ አባባ ሕዝብ የሚያውቀውን' 'አረመኔው ግረማ ከበደ' በሎ ሰም ያወጣለትን ነፍስ ገዳይ በመጽሐፋቸው ያላወጡ፣ ጓዶቻቸው በሴቶች ላይ ያደረሱትን በደል ይጽፋሉ ብዬ አልጠብቅም። ምክንያቱም ባጠቃላይ አቀራረባቸው ሚዛኑን ያልጠበቀ፡ የኢትዮጵያዊነት ጨዋነት የጎደለው ነው። ኢሕአፓ የፖለቲካ ድርጅት ነው፤ የራሱ የሆኑ ብዙ ሰህተቶችን ፈጽመሟል፤ በሀገራችን በግለጽ መነጋገሩ ቢኖር ኖሮ አፍረጥርጠን የሁሉንም ወገን እናየው ነበር፤ሆኖም ኢሕአፓ የመንግሥት ሥልጣን አልያዘም፤ በትግሉ ግን የሴቶችን ድረብ ጭቆና ተቀብሎ በተግባር አውሏል፣ ድርጅቱን ጭላት እቀባለሁ ብለው ማስረጃ ለማያቀርቡበት ጉዳይ የታጋይ ሴቶችን ሰም ማጉደፉ ለማንም አይበጅም። 'ለሴተኛ አዳሪነት በጎረቤት አገሮች አሰማራ፣' ሲሉ፤ ከየትኞቹ የጎረቤት አገሮች? ሰውዬው ያለው ነገር መጣ፣ 'ዋሽልኝ እዋሻለሁ ነፉስ በወጥመድ እይዛለሁ፤' ይመስላል፤

ኢሕአፓ በኤኮኖሚው መሰክ የፈጸመውን አሻጥር እንየው፣ በመንግሥት እርሻዎችና በመገልገያ መሣሪያዎች ላይ ያደረሰውን ውድመት ገልጸዋል፣ የመንግሥት እርሻ የሚባል ነገር የለም፤ ከመሬት አዋጅ በፊት ትልልቅ እርሻዎቸ የግለሰቦች ነበሩ፤ ሰለተወረሱት ሰፋፊ እርሻዎች የሚያወሩ ከሆነ መሬት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሲውል እርሻ መሆኑ ቀርቶ ያደረ ማሳ ነው የሚሆነው፤ ለዚህ ተጠያቂ የሚሆነው ያለ ዕቅድ የሚሰራው መንግሥት ብቻ ነው። የሀገር ንብረት መውደም የመሬቱ ማደር ያሰቆጫቸውና አንድ ነገር እናድርግ ብለው ነጋሽ ሣህሌ ከአጋርፋ ባሌ፣ ታደሰ ይርገጤ ዶዶላ ባሌ ይነሣሣሉ፤ ሁለቱም የኢፒድ ሠራተኞች ነበሩ፤ የማሳው ማደር የትራክተሩ መውደም የሚመለከትው የእርሻ ሚኒስትር ተወካዮችን ነበር፤ የስዊድን መንግሥት ለኢፒድ በሚልከው ባጀት ሠራተኞቹን አሰተባብሮ የተወረሰውን ማሳ በተወረሱት ትራክተሮች አርሶ ስንዴ ዘራው፤ ይህን ያደርግ የነበረው ከካድሬዎች በመሸሽግ ነበር፤ 200000 ኲንታል ስንዴ አምርቶ ከማጋዘን አግብቶ ለቤሔራዊ ሐብት ልማት አሰረከበ። ባሌ በክረምት መንገዱ አስቸጋሪ ሰለሚሆን ባአስቸኳይ እንዲያጓጉዙ ነግሯቸው ተመለሰ፤ አስር ሺ ኲንታል በማጋዘኑ ቀርቶ ስለነበር በፍሳሽ ጥቂት ኲንታል ይበላሻል፤ ገበሬዎች ይህን ስንዴ ከሰብል በኋላ

ሊተኩለት ለዘር ይጠይቁታል፣ በራሱ ለገበሬዎቹ መሰጠቱ ያስጠይቀኛል በማለት በአካባቢው የደርግ አባሉ ይመጣል ሰለሚባል ሲመጣ ጠይቁት ይላቸዋል፣ የደርግ አባሉ ይመጣል ይጠይቁታል፣ ማነው ያስቀመጠው ይላል ነጋሽ ነው ይሉታል፤ በ1968 ዓ ም ክረምት ላይ በባሌ ክፍለሃገር ኢሕአፓ የኤኮኖሚ አሻጥር ሥራ ተብሎ በቴሌቭዥን በተደጋጋሚ ለአዲሰ አበባ ሕዝብ ቀረበ፤ ነጋሽ ሣህሌ በኢሕአፓ አባልነት በኤኮኖሚ አሻጥረኝነት ታሰረ፤ ደራሲው ገጽ 315 ላይ የእርሻ ሚኒስትሩና የቤሔራዊ ሐብት ልማት ሚኒስትሩ መታሰራቸውን ገልጸዋል፤ መንግሥቱም ይህን ያልተጣራ ነገር ይዞ ቡራከረዩ ሲል እነ መቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ ጅንራል ተፈሪ ባንቲም ቁም በአንደኛ ብለው ሥልጣኑን የተፈታተኑበት መነሻው ያ ነበር። ነጋሽ መንግሥትን ቤሳ ቤቲን ሳያስወጣ ላመረተው ምርት ማስረጃዎቹን ቢያቀርብም ሊቀበሉት አለፈለጉም፤ ለእውነት ብሎ የቆመ አልነበረም፤ ነጋሽ አሥራ አራት ራሱን በአንድ ጉድጓድ በጥይት ተደብድበው ተገደሉ፣ አንዱ አብረው የተገደሉት፣ የሐረር ሕዝብ እንደራሴ ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ፣ ወንድም ናቸው፣ የታወቁ አርበኛ ነበሩ፣ ሃይሌ ዘለቀ ይባላሉ። አስከሬናቸው ያረፈበት ምድር ላይ የኢሣፓ ጽፈት ቤት ተሰርቷል፣ ባሌ ጎባ ስትደርሱ Welcome to Bale Goba ከሚለው በስተግራ ታገኙታላችሁ። ታደሰ ይርገጤም የተወረሱ ማሳዎች ለጊዜው በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ቆይተው፣ ባጅት ተመድቦላቸው ይታረሱ፣ የከተማው ቦዘኔ በቀን ሠራተኛነት ይሰራ፣ ቢል ለገበሬው አንዳይከፋፈል አሸጥር ነው ብለው ሊያስሩት ሲያሴሩ አምልጦ አዲሰ አባባ ቢገባም አላመለጠም፣ ይዘው ገለውት ካሳቺስ እርሻ ሚኒስተር ጽፈት ቤት በራፍ ጣሉት። እነዚህ ወጣቶች መሥሪያ ቤታቸው እነደተዘጋ ለድህረ ምርቃ አሜሪካ እንዲሄዱ አለቃቸው አመቻችቶላቸው ነበር፤ ሀገራችንን በመስቀለኛ መንገድ ላይ ትተናት አንሄድም ብለው የቀሩ ናቸው፤ አለቃቸው ዛሬ ከስደት ተመልሰው ሀገር ቤት ይኖራል።

በደርጎች ውስጥ ኢሕአፓ ቀውስ በመፍጠሩም ደራሲው ይወቅሳሉ፣ እርሰ በእርሳቸው ለሥልጣን ሽኩቻ ባደረጉት መገዳደልም ኢሕአፓን ተጠያቂ ያደርጋሉ፤ ተጨባጭ ማስረጃ አያቀርቡም፣ በአንድ በህቡዕ በሚሰራ ድርጅት ውስጥ ግለሰቦችን አባል ናቸው ማለት ይከብዳል፡፡ በደርግ ውስጥ የሚታየው በችሎታና በሥራቸው በታወቁና ሻለቃ መንግሥቱ ያሉት ሁሉ ይሁን በሚሉ መካከል ነበር፤ ኢሕአፓም ደርግም የሚከተሉት ርዕዮተ ዓለም ሶሻሊዝም ነው፤ ከደርግ ውስጥ የነበሩት ሊሂቃኑ የኢሕአፓን ሰለ ሶሻሊዝም የሚሰጠውን ትንታኔ ሊወዱት ይችላሉ፣ ግን አባል ናቸው ማለት እንዴት ይቻላል? ለምሳሌ የመኢሶን አባል የሆኑት አቶ አበራ የማንአብ በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሃን በሰጡት ቃል መጠይቅ መቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌና እርሳቸው አንድ ቤት እንደሚኖሩ ነው፤ ሰለመሬት ጉዳይ አብረው እንደሰሩ ተናግረዋል፣ ደራሴው የመቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌን ቀደኛ የኢሕአፓ አባል አድርገው አቅረብውታል። በግልጽ የሚታየውን በዕውቀታቸው በሚተማመኑትና በቲፎዞና በአድርባዮች ስብስብ በሚመሩት በሻለቃ መንግሥቱ መካከል ያለውን ቅራኔ ከመግለጽ ተቆጥበው ማረጋገጫ በማይሰጡበት ጉዳያ ላይ አተኮረዋል።

ኢሕአፓን፣ ሀገር በማስገንጠል፣ በፀረ-ኢትዮጵያዊነት፣ ከውጪ አገር አበሮ ሀገራችንን በመውጋቱ፣ በገዳሐሪፍና በሞቅድሾ ቢሮች በመከፈቱ ያወግዙታል፤ ደራሴው ሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት መንግሥታችው ወያኔ ኤርትራን ለማስግንጠል ይዋጋ እንደነበር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይነግሩት ነበር። የወያኔ መስራችም አቦ ስህባት ነጋ ኤርትራን በማስገጠላቸው ጃሎ መገን ሲፎክሩ ይሰማሉ፤ ደራሴው በምን መረጃ ኢሕአፓን አስገጣይ እንዳሉት አላብራሩም ፣ ይህን በታሪክ የሚያስወቅስ ተግባር በኢሕአፓ ላይ ሲለጥፉ ማስረጃ ማቅረብ ግድ ይላቸው ነበር፤ ወያኔን ከታሪክ ተወቃሽነት ለማዳን ሲሉ ለሕብረቤሄር ይታገል የነበረን ድርጅት አስገንጣይ ማለቱ ማንንም አይሳምንም። ከጥላቻ በመነሳት ብቻ ፍትው ብሎ የሚታየውን ሐቅ ማወላገድ ታሪክ ማስተማር አይሆንም፣። በተጫባጭ ዛሬ የሚታየው ሕዝቡ ወያኔን ፀረ-ኢትዮጵያ እያለ ሲያወግዝ ነው፣ ካለ ወደብ አስቀረኝ፣ ለም መሬቴን ሸጠ፣ ሀገር ቆርሶ ለባዕድ ሰጠ፣ የዘር ፖለቲካ አሰፋፋ፣ ወገን ከወገኑ አጣላ የሚሉትን ምክንያቶች ይሰጣል፤ ኢሕአፓ ሥልጣን ይዞ ሀገር ሣይመራ ደርግ በመፋለሙ ብቻ ፀረ-ኢትዮጵያ ሊሆን ይችላል? ወይስ ወያኔን ከየታሪክ ተወቃሽነትን ለማዳን ሆን ተብላ ሰሞኑን የቀረበች ናት? ኢሕአፓ በሞቅድሾ ቢሮ አልነበረውም፣ በሱማሊያ በኩል ከሀገር ወጥተው በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሊመሰክሩ ይችላሉ፤ ፤ ከደርግ ጋር ተሰልፈው ነፍስ ያጠፉ ጭምር ለስደት ሱማሊያ ሲገቡ ኢሕአፓ ነን ነበር የሚሉት፤ እነሱ ሳይቀሩ ሊመሰክሩ ይችላሉ። በሀገር ቤት አንድ አባባል ነበር፣ ‘ዲሞክራሲያ’ እንደ ወንጂ ሰኳር በአይሮፕላን፣ በመኪና፣ በአጋሰስ፣ በአህያ፣ በግመል ተጭና የገጠር ከተማዎችን አዳርሳለች። ነጋዴው መርካቶ የተበተነን ወረቀት ለእርሱ የሚጠቅመው ነገር ያለበት መስሎት ከመንደሩ ይዞት ይመጣል። ብዙ ጊዜ አሰተማሪዎችን ወይም የተማሩ ልጆቹን ያስነብባል። የኢሕአፓ ልሳን መሆኗን ያወቁ አንዷን ቅጽ እንኳን ያነበቡ ኢሕአፓ ነን ማለት ይጀምራሉ። ‘ዲሞክራሲያ’ በግመል ተጭና አጋዴን ለመግባት ማን ይከለክላታል? የዕድገት በሕብረት ዘማቾችንም አንርሳ፤ ደርግ በከተማ ኢሕአፓ ላይ ሲዘምት በሐረር፣ በድሬደዋና በጅጅጋ

የነበረው ወጣት የኮበለለው ወደሱማሌ ነው፣ ጥቂት ሱማለኛ ተናገሪ ወጣቶች በምዕራብ ሱማሌ ስም የሚቀሳቀሱትን ቡዱኖች ተቀላቅለዋል፤ የኤርትራ፣ የትገራይ ወጣቶችም አድርገውታል፤ እነዚህን ነበር ደራሴው ከውጭ አገር አብሮ ሀገሩን ወጋ ብለው ያቀረቡት፤ በዚያን ወቅት መሣሪያ የታጠቀ ቡድን ደርግን እዋጋለሁ ይል እንደሆን እንጂ ኢትዮጵያን እዋጋለሁ የሚል አልነበረም። የኢሕአፓን መጨረሻ በዚህ ልቋጨው፣ አንድ ወጣት  በኢሕአፓነት ሲፈለግ ከአካባቢው ለሁለት ዓመት ከተሰወረ በኋላ ወደ መንደሩ ይመጣል፣ የዘመዱ ጓደኛ የሆኑ  አሮምኛ ተናጋሪ በአሮመኛ ‘ ወራ ከረራ ደጋለሙ’ በቀዬው ላይ ቆሞ የሚዋጋው ክፍል ነህ? ካሉ በኋላ፤ አዎ ስላቸው ‘ወራኒ ዴሲ ገሊ አዴሲ’ ወግተህ ሽሻና አውራ ግባና! ጠላትህን አቁስለህ ገብተህ ታወራለህ፤ ምን ዋጋ አለው ማለታቸው ነው።

ሰለ የመላው የኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) 341 ላይ የመኢሶንና የደርግን ፍቺ መቃረቡን እናያለን፤ የመኢሶን አባላት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያምን እጁን ይዘው፣ የሶሻሊዝምን ሀ ሁ እንዳላስቆጠሩት ዕውቅት ከሥልጣን ይመጣ ይመስል፣ ለመኢሶን አባላት ‘ሰለአገራቸው ወቅታዊ ፣ ወታደራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ገለጣ አደረጉላቸው’ ይሉናል።ከውጤቱ እንዳየነው ሊገላቸው እንዳስፍራራቸው ነው። በዚሁ ገጽ ላይ የመኢሶን አባላት በሀገሪቱ ተበትነው ለሚገኙት አባሎቻቸው ሣያስታውቁ፣ የሱማሌ ጦር ወደ መሐል ሀገር እየገለገሰ መምጣቱን አይተው በፍረሃት ፈረጠጡ ይሉናል፣ ከአባላቱ አንዱ ብልጣ ብልጡ አሥር ሺ የኢትዮጵያ ብር ይዞ በቦሌ መኮብለሉን አልሸሸጉም፣ በመጽሐፋቸው ውስጥ የሸሸጉን ነገር ቢኖር ግን፣ ሀገር ወዳዱ እያሉ የሚያቆለጳጵሱት ፕሬዘዳንት መንግሥቱ ኃይለማሪያም የወያኔና የሻዕብያ ሀገር አጥፊ ሽፍቶች ወደ መሐል ሀገር ሲገሰግሱ አይቶ፣ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሆነ ሠራዊት ከነሙሉ ትጥቁ በትኖ፣ መጠኑን ያልነገሩንን ገንዘብ ዘርፎ፣ ሀገርና ሕዝብ  አጥፍቶ፣ አይሮፕላን ጠልፎ ወደ ዙባቤ ሰለጠፋው  ያሉን ነገር የለም። ይበልጥ ያተኮሩት በሕይወት ሰለሌሉት፣ እንደ ዱኩላ አድነው ሰለገደሏቸው፣ የፍጥኝ አስረው ሰለረሸኗቸው፣ ገድል ነው። ሰለ መኢሶን ድርጅት አባላት ያቀረቡት ግንዛቤ ማናቸውን የድርጅ አባላት ይመለከታል፤ ‘የመኢሶን አመራር አባላት ሁሉም በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ ይሁኑ እንጅ አገራቸውን በጥልቀት አያውቁም፤’ የደርግ  አባላት ደግሞ ይበልጥ ሀገሪቱን አለማወቃቸውን ዘለውታል።

ስለወዝ ሊግ መስራቹ ዶክተር ሰናይ ልኬ ብቃትና ስዕብና  ጥሩ አድርገው  አቅርበውታል፣ ከሠራዊቱ ውስጥ ብቃት ኖሯቸው ለወዝሊግ አባላንነት የተመለመሉትን ገልጽዋል፣ እርሳቸው የእርሱ ምልምል መሆናቸውን አልነገሩንም፤  ሌሎች ጓዶቻቸውን  በሰደድ ድርጅት ሰርጎ ገብነት አጋልጠው ለመንግሥቱ ኃይለማሪያም  ግድያ አሣልፈው ሰጥተዋቸዋል፤ ሰለጓዶቻቸው አሟሟት ያሉት ነገር  የለም።

ደራሲው እንዳቀረቡት የአብዮታዊ ሰደደ መስራችም  ሊቀመበርም መንግሥቱ ኃይለማሪያም መሆናቸውን ነው። ለምን እንደመሠረቱት በገጽ 345 ላይ ገልጽውታል፣ የዶክተር ሰናይ ልኬን ከወታደሩ ውስጥ በዕውቀት ላቅ ያሉትን  ለወዝሊግ መመልመሉ ለሥልጣናቸው አሰጊ ሆኖ ሰለአገኙት መሆኑ ግለጽ ነው፤ ደራሲው አደጋ ካለው ወዝሊግ ወደ ሰደድ ያደረጉትን ሽግግር  በለውሳስ አለፍውታል፤ የድርጅቱን ፕሮግራም ማን እንዳዋቀረው አልነገሩንም፤  መቼም በስድስት ወር ሀ ሁ መንግሥቱና ለገሰ አስፋው ሊሆኑ አይችሉም፣ እርሳቸው ቢሸሽንም እኔ ልገራቸሁ፣ ገጽ 354 ላይ ከአሲንባ ከኢሕአፓ እጃቸውን የሰጡ ብለው የአምስት ግለሰቦችን ስም ዝርዝር ጽፈዋል፣ ከነዚህ ውስጥ የሊቀመበሩ የቤተሰብ አባል ነው የሚባለውን  የአያሌው ከበደን ስም ሆን ብለው ዘለውታል። የአብዮታዊ ሰደድን ያዋቀሩት ተስፋዬ መኮንንና አያሌው ከበደ ዋናው ተዋናኞች ነበሩ፤ አያሌው ከበደ በየክፍለሃገሩ እየዞረ በአንድ እጁ የማሌሪድ ልሳን የነበረውን ሪቮሊሽንን ሲያድል፣ በሌላ እጁ የሰደደን ፕሮግራም እያደለ ለድርጅቱ ብሮክራቱን ይመለምል ነበር።

እንደ ደራሲው አቀራረብ  በግልቡ ካየነው፣ ሰደድና ማሌሪድ የተለያዩ ድርጅቶች ሊመስሉን ይችላሉ፣ ሰደድ ሲባል የወታደሩን ክፍል ስለሚያጸባርቅ፣ የቡርጌሱን ምኞት ለመጠበቅ  በስላቅ ማሌሪድ ተቋቋመ፣ በእርግጥ የሥልጣኑን የአንበሳውን ድርሻ ያለው ሰደድ ነበር፣ ሰለዚህ ማሌሪድ  የሰደድ ዣንጥላ ያዥ ነበር።

የኢትዮጵያ ጭቁኖች አበዮታዊ ትግል(ኢጭአት) ከገጽ 357-359 ይህ ድርጅት በተቀሳቀሰበት አካባቢዎች የፈጸማቸው ን እኮይ ተግባሮች ጽፈዋል፣ መታወቅ ያለብት በህቡዕ ከሚቀሳቀሰው ከኢሕአፓ በስተቀር የቀሩት በመንግሥት ዕውቅና የሚሰሩ ናቸው፤ ሰለዚህ ለተፈጸሙት ጥፋቶች ተጠያቂው የራሳቸው መንግሥት ነው። ለምሳሌ በባሌ ክፍለሃገር የተመደቡት የደርግ አባላትና የኢጭአት ካድሬዎች እጅና ጓንት ሆነው ሠርተዋል፣ አቆርቋዥ ፣ አደሃሪ ፣ ነፍጠኛ፣ ኢሕአፓ በማለት ማገርና ግድግዳ ሆኖ  ሀገሩን  አስከብሮ  የኖውን የሕብረተሰብ ክፍል እየመረጡ አጥፍተዋል፣ በጋራ የሚገሉት፣

የሚያስገድሉት አከተመ ፣ አካባቢውም የጅግና መካን ሆነ ፣ ሕዝቡም በየአቅጣጫው ወደ ጫካ ገባ፣ አቅም ያለው ሱማሌ ሄዶ በሱማሌ አቦ ስም መሣሪያ ታጥቆ በጫካ መሸገ፣ በደርግ አባሉና በኢጭአት አባላት መካከል የሥልጣን ሽኩቻ ተፈጠረ፣ 'የኢጭአት ካድሬዎች 'መጤ፣ ነፋጠኛ'' እያሉ የአማራኛ ተናጋሪውን እንዲባረር ቅስቀሳ እንዳደረጉ' ፤ ካለደርግ አባሉ እውቅና የሚደረግ ነገር የለም። 'መጤ' የሚለው ቃል የመጣው የሸዋው ኦሮሞ ፣ የእስልምና ተከታይ በሆነው ኦሮሞ መሬት ላይ ሰፍሮ በኩል አራሽነት ያርስ ነበር፤ ከመሬት አዋጅ በኋላ በመሬት ድልድል ምክንያት በተፈጠረው ግጭት ብቅ ያለ ቃል ነበር፤ ደራሴው አጋነውታል። በደርግና በኢጭአት መካከል ቅራኔው ሰፍቶ ኢጭአቶች በየቅጣጫው መኮብላቸውን እናያለን፣ በሐረርጌ በባሌ በአርሲ ክፍለሃገራት የትጥቅ ትግላቸውን ለማድረግ መሰማራታቸውን ጽፈዋል፣ በባሌና በአርሲ ዋቆ ጉቱ ከሚመሩት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ለመቀላቀል መረባቸውን መዘርጋታቸውን ገልጸዋል፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የሚሉት ደርጅት የትጥቅ ትግል የሚያካሄድ በሐረር፣ በባሌና በአርሲ አልነበረም። ዋቆ ጉቱ በባሌና በአርሲ፣ ሼክ ኢብራሂም ቢሊሣ በሐረርጌ በሱማሊያ መንግሥት የሚረዳው 'የሱማሌ አቦ' ንቅናቄ መሪዎች ነበሩ፤ በእርግጥ ጀራ የኢጭአት አባል ባሮ ቱምሳንና ሌሎችን እርግጠኛ አይደለሁም፤ 'ኦሮሚያ' የሚለው ሰም የተፈጠረው ወያኔ ሀገሪቷን ከተቆጣጠረ በኋላ ነው፤ ጃራ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኦሮሞ ነው፣ 'ኦሮሚያ ኢስላሚያ' የሚል ድርጅት አልነበረም፣ የነበረው በሱማሊያ የሚረዳው የሱማሌ አቦ ድርጅት ነው፣ የነባሮ ቱምሳ ችግር ሊሆን የሚችለው በሱማሌ አቦ ውስጥ ከተሰገሰጉት የሶማሊያ ሰላዮች ነው፤የተማረ ሰው አይፈልጉም፣ የክርሰትና ሃይማኖት ተከታይ ከሆነ በሰላይነት ይጠሩጥሩታል፣ በተለይ ዐርብ ሮብን የማይጾም፤ እነርሱ ያረዱትን ሥጋ የሚበላ ከሆነ በአይን ቁራኛ ይጠበቁታል፤ መጨረሻው ሞት ሊሆን ይችላል። እነባሮ ቱምሳን የዘመኑ አማሮች ወይም ዴጤዎች እገምታለሁ፤ ምክንያቱም ከባሩ ቱምሳ ጋር የተገደለው የባሌ ክፍለሃገር ምክትል አስተዳዳሪ የነበረው መገረሣ በሪ ይገኝበታል፤ ባሌን ሲያስተዳድር ከመስኪድ ሄዶ 'እስላም ያረደው ክርስትያን ያረደው ብሎ የከፋፈሏችሁ አዳሃሪያን ናቸው' ብሎ በመቀስቀሱ ትልቅ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፤ በሱማሌ አባ ውስጥ የሶማሊያ ሰላዩች ካለሆኑ በስተቀር መሪዎቹ ለኦርቶዶክስ ተከተዮችና ለቤተክርስትያን ትልቅ ክብር አላቸው። ያም ያለምክንያት አይደለም፤ በኢትዮጵያ ላይ ያዣበበው ሶሻሊዝም ሁለቱንም የሀገሪቱን ሃይማኖቶች ያጠፋቸዋል ብለው ሰለሚያሰቡ ነው። ደራሲው 'የኢጭአት ልሳኑ ነፃነት ያሉት' የአማርኛው ፍቺ ነው፣ ልሳኑ 'ቢሉሱማ' ይባል ነበር፤ በተከታታይ ከሦስት እትሞች በላይ አላወጣም። ኢጭአትን ለማጋለጥ ብለው፣ ስለ16ኛው ክፍለ ዘመን የግረኝ መሐመድ ወረራ ትንታኔ በመስጠት፣ ሌላ ሰህተት ውስጥ ገብተዋል፣ በመጀመሪያ ግራኝ መሐመድ ቤተክሪያተኖችን፣ የሀገር ቅርጾችን፣ ክርስቲያኖችን አጥፍቷል፣ በወረራቸው አካባቢዎች መሲኪድ አሰርቶ ቁራን እንዲሰበክ አላደረገም፣ ሰለዚህ ሃይማኖት አላስፋፋም። ኦሮሞች ግራኝ መሐመድን እየተከተሉ የወረራ ዘመቻ አካሄዱ፣ አማራውንና ሌላውን ጎሳዎች አባረው የያዙትን አካባቢ ኦሮሞ አደረጉት የሚል ትንታኔ ሰጥተዋል፣ በአንድ ጎኑ ሰለእስልምና መስፋፋት ይናገራሉ በሌላ ጎኑ ሰለኦሮሞ ቤሄር አመጣጥ ይገልፃሉ ይህ ሁሉ የኢጭአትን ስህተት የመንግሥታቸውን ትክክልኝነት ለማሳየት ነው፤ መታወቅ ያለበት በ16ኛው መቶ የነበረችው ኢትየጵያ የዛሪቱ ኢትዮጵያ ናት፣ '' መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ'' ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም 2005 ዓ ም ከገጽ 207-211 ያሉትን ካርታዎች መመልከት ይበቃል። ያንን ካርታው ላይ ያለውን ሀገር ወሰን አሰከበሮ እሰከዛሬ ያቆየው የአንድ ጎሳ አባል እንዳልሆነ እናውቀዋለን። የውጭ አገር ታሪክ ጻፊዎች በፃፉት ላይ ተመርከዞ ከትንታኔ መግባቱ ጥቅም የለውም። ሰለግራኝ መሐመድ ከተነሣ በሕብረተሰባችን የሚነገረው አፈ ታሪክ ያሳምነኛል፣ የግራኝ መሐመድን ኢትዮጵያዊነት ይቀበላሉ፣ በቤተክርስትኖችና በምዕመናኑ ላይ ያካሄደው የግል ብቀላ እንደሆነ ያቀርቡታል፣ ቄስ የነበረው አባቱ እስላም ከነበረችው እናቱ ፍትቶ ሥጋ ፈጽሞ ጥምጥሙ መስሎት ጉፍታዋን ጠምጥሞ ለቅዳሴ በመግባቱ ቄሶች አባቱን በማቋሚያ ቀጥቅጠው ስለገደሉበት ለብቀላ ያደረገው ጦርነት ነው፣ ይባላል። ሰለአማራውና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሲነሣ ሰለ ቀድሞው ጠቅላይ ሚነስትር መለስ ዜናዊስ የሚነገር ነገር ይኖር ይሆን?

ምዕራፍ 17 ላይ ከገጽ361-396 አገራችን በሶማሊያ መወርሯን ያትታሉ፣ ደርግ የሶማሊን ወረራ በማስቆሙ ራሱን ማሣያ አድርጎ አቅርቧል፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሶማሌ ወረራ አዲስ ነገር አይደለም፤ ብዙ ጊዜ ሞክራ ሕዝቡ ባለው መሣሪያ ከሠራዊቱ ጋር ተሰለፎ አሣፍሮ መልሷታል። አሁን ከኢትዮጵያ የተሻለ መሣሪያ ታጥቃለች በማለት የውጭ ሀገር ሠራዊት የሚያስጋብዝ ለመሣሪያ ሀገሪቱን መለወጥ የሚያኮራ አይደለም። ዘይድ ባሬ ኢተዮጵያን የወረረው በቀደማዊ ኃይለሥላሴ ላይ በወታደሩ የተፈጸመው መፈቀለ መንግሥት በእኔም ይሆናልን በመፍራትከራሱ ላይ አቅጣጫ ለማስለወጥ ያደረገው ወረራ ነው፤ የመንግሥቱም ታላላቅ ሰዎችን ጨርሶ ታላቅ መስሎ ለመታየት ያራገበው ጦርነት ነው። ኢሕአፓ በልሳኑ 'ዲሞክራሲያ' 'ዘይድ ባሬና መንግሥቱ አንድ ናቸው' ያለውን በተግባር አየነው። ገጽ 392 ላይ የአሜሪካው ፕሬዘዳንት የነበሩት ጂሚ ካርተር ያሉትን እጋራለሁ፣ሶማሊያ ሳትሆን እናንተ ናችሁ ሽብር ፈጣሪዎች ያሉት ትክክል ነው። የራሱን ቤት ያቃጠለ እብድ ሌላው እብድ የቀረውን ለማቃጠል ቢመጣ ተወቃሹ ማነው?

ምዕራፍ 18 ላይ የሶማሊያንና የሱዳንን የዘሩትን አጨዱ ብለው ሲያጣጥሉ በጥንታዊቱ ሀገር  እርሳቸው ጠቅላይ ሚንስትር ሆነው ያስተዳደሯትን ኢትዮጵያ ከሁለቱም በታች እንድትሆን አመቻችተዋት ለወያኔ ማስረከባቸውን አሁንም አልታያቸውም።

ምዕራፍ 19 መንግሥታቸው ሰለአመጣው የኤኮኖሚ እድገት አንዳንድ ፎቶዎቹን በመለጠፉ አሣይተዋል፤ ዞር ብለው ደግሞ ቀጣይነታቸውን ገምግመው ቢሆን  እድገት ማለት ምን እንደሆን ይረዱ ነበር። የሰዎችን ሰዕባዊ መብት መሐከል ያላደረገ ልማት ሕብረተሰብን አይለውጥም፣ በየኤኮኖሚ እድገት ሊኖር አይችልም፤ ዕድገት ከነፃ አስተሳሰብ የሚመጣ ወጤት ነው፤ ፍትህ በሌለበት ስዎች በነፃነት ሐሣባችውን በማይገልጹበት ሕብረተሰብ፣ የኤኮኖሚ እድገት ሣይሆን፣ ባርነት፣ደህነት፣ስደት፣ ወርደት የመብት ረገጣ ጎልቶ ይታያል ይህን ደራሴው ከአርባ ዓመት በኋላም ያዩት አይመስልም።

ዛሬ  በ2006 ዓ ም  ላይ ሆነን  ወደኋላ ተመልሰን በ1966 ዓ ም ከነበረበት የሕዝቡ ኑሮ ተሻሽሏል ወይስ ብሷል?  ደራሲው አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ተመክሮአቸውን አካፍለውናል፣ ግለሰቦች ነገሮችን የሚያዩበት የራሣቸው መነፅር አላቸው፤ አንደኛው መነፅር መጽሐፍ ነው። ደራሴው ‘እኛና አብዮቱ’ ን እንደመነፅር ተጠቅመውበታል፣ ሊመሰገኑ ይገባል። ሆኖም ግን ሀገር ለማስተዳደር ትልቁ መነፅር ሕዝብ ነው፤ አልተጠቀሙበትም፣ ያንን መነፅር የተጠቅሙት  ዕምዬ ምኒሊክ ነበሩ።

ታደለ መኩሪያ
tadele@shaw.ca